<u>**የኢትዮጵያ ሚሊኒየም የብሔራዊ ሰላምና ዕርቅ ጥሪ**</u>
<u>**ከኢንጅነር ግዛቸው ሽፈራው (የግል አመለካከት)**</u>
<u>**ከቃሊቲ እስር ቤት**</u>

***የሁላችን የሆነችው ኢትዮጵያ ከ 3000 ዓመት በላይ ታሪክ ያላት ሀገር ናት በዚህ ስልት ከክርስቶስ ልደት በፊት አንድ ሚሊኒየም ከክርስቶስ ልደት በኋላ ሁለት ሚሊኒየም አሳልፋለች። ኢትዮጵያ የራሷ ፊደልና የዘመን አቆጣጥር ባለቤት መሆን መቻሏ ከበርካታ የዓለም አገሮች ቀደምነት ያላት ታሪካዊ አገር ያደርጋታል የራሷ የሆነ የዘመን አቆጣጠር ስላላትም እነሆ በአሁኑ ጊዜ የሚሊኒየም በአል ለማክበር መንግስትና ውስን ሰዎች ደፋ ቀና እያሉ ነው። በፌደራልና በክልል ደረጃም ሚኒሊየሙ የሹማምንቶች ቀዳሚ ስራ ሆኗል የመንግስት አፈቀላጤ የሆኑትም መገናኛ ብዙሃን ሰፊ የፕሮፓጋንዳና የማስታወቂያ ሽፋን እየሰጡ ይገኛሉ። የኢትዮጵያ ሚሊኒየም መከበር በመሀርና በታሪክ አንጻር የሚደገፉ ጉዳይ ሲሆን አላማዎቹ ሒደቶቹና ድርጊቶቹ ግን በጥቂቱ የሚከተሉትን አገራዊና ህዝባዊ ጥያቄዎችን የሚያስነሱና የሚጋብዙ ናቸው። ሀቀኛ ውይይትና መልስም ይፈልጋሉ።***

1. ***የሚሊኒየሙ በዓል አከባበር የሁሉም የኢትዮጵያውያን የጋራ መንፈስና አንድነት ምን ያህል ይዟል?***
2. ***የሚሊኒየሙ አከባበር በአገር ውስጥና በውጭ ሀገር ያሉትን ኢትዮጵያውያን እያስተባበረ ነው? ወይስ እየከፋፈለ?***
3. ***የሚሊኒየሙ በዓል በእርግጥ የኢትዮጵያ ህዝብ በዓል እየሆነ ነው? ወይስ የኢህአዴግ መንግስት የፕሮፓጋንዳ በዓል እያደረገው ነው?***
4. ***ሚሊኒየሙ ለአገሪቱ ህልውና ፈታኝ የሆኑት የፖለቲካ ችግሮች የሚፈቱበትን አመቺ ሁኔታዎች ለምን አይፈጥርም?***
5. ***የኢትዮጵያ ሚሊኒየም በዓል አደረጃጀት ፖለቲካ ፖለቲካ እየሸተተ እውነት ከፖለቲካ ገለልተኛ ነው?***
6. ***የሚሊኒየሙ በዓል በምርጫ ላይ የተከሰተውን የፖለቲካ ቀውስ ሽፋፍኖ ሊያቀርብ ነው? ወይስ ለብሄራዊ ዕርቅና የመቻቻል ፖለቲካ መሰረት ለመጣል ምክንያት ለመሆን ይችላል?***
7. ***የ2000 ዓመት የሚሊኒየም ጉዞ ለኢትዮጵያ ህዝብ የፖለቲካ ኢኮኖሚና ማህበራዊ ልማት ምን እንዳስገኘ በሐቅ ለመገምገም ለምን አልተሞከረም?***
8. ***ከተጨባጭ የአገራዊ ልማትና ህዝባዊ እድገት አንጻር ሚሊኒየሙን የምናከብረው በኩራት ነው? ወይስ በሐፍረት? በደስታ ነው ወይስ በሃዘን?***
9. ***ሚሊኒየሙ የአዲስ አበባና የክልል ከተሞች በዓል ነው? ወይስ የገጠሩንም ድሃ ህዝብ ይመለከታል?***
10. ***የኢትዮጵያ ህዝብ ወደ አዲሱ ወይም 3ኛ ሚሊኒየም ሊሸጋገር ምን ራዕይና ተስፋ አንግቦ ነው?***
11. ***የዛሬ 7 ዓመት የተከበረውን የፈረንጆች ሚሊኒየምን መሰረት አድርጎ ዓለም በ2015 የሚገኝ የሚሊኒየም ልማት ግብ*** (MOG) ***አስቀምጧል። በዚህ አንጻር የኢትዮጵያ ሚሊኒየም የዲሞክራሲና የልማት ግቦች ለምን አልተቀመጡለትም? ረሃብና ድህነት በምን ያህን ጊዜ ከኢትዮጵያ ይጠፋሉ? የእነዚህ ጥያቄዎች መልሶች የተለያዩ ሐሳቦች የሚጭሩና ችግሮች ሚሊኒየሙን ስናከብር ልዩ አትኩሮት ሰጥተን መፍትሄ ልናስገኝላቸው ይገባል ለአገሪቱ ውስብስብ የፖለቲካና የልማት ችግሮች ዘላቂ መፍትሄ ማስገኘት ሁሉም ኢትዮጵያውያን በሚሊኒየሙ የሚተባበሩበት የዜግነት ግዴታ መሆን ይኖርበታል። ሚሊኒየም የኢትዮጵያውያን ጥቂት በጎ ታሪካዊ ገጽታዎች ባሻገር እጅጉን በአለም አቀፉ ደረጃ ጎልቶ የሚታየውን አሳፋሪ ገጽታዋን የምለውጥበትና ለቀጣይ አስተማማኝ መፍትሔ እንደ አንድ ህዝብ ፣ እንደ አንድ ሀገር በአንድ መንፈስ የምንረባበርበት አዲስ ምዕራፍ መሆን ይገባዋል የሚል እምነት አለኝ።***

የኢትዮጵያን ሚሊኒየም ስናከብር በተቀዳሚ ማሰብ የአለብን ለዘመናት እየተረገጠና እየተጨቆነ ያለውን የኢትዮጵያን ድሃ ህዝብ ሁኔታ ነው፡፡ ያለፈው ሚሊኒየም ኢትዮጵያ ብዙ እረሃብተኞች፣ ብዙ ለማኞች፣ ብዙ ስራአጦች፣ ብዙ በሽተኞች፣ ብዙ ጎዳና ተዳዳሪዎችና ብዙ ስደተኞች ማፍራቱ አለም ያወቀውና ፀሃይ የሞቀው ሀቅ ነው፡፡ በኦክስፎርድ ዲክሽነሪ (በመዝገበ ቃላት) ኢትዮጵያን በራህብተኛነት ምሳሌ አድርጎ ማቃረቡ የምግብ ችግራችንን የሚመለከት ያለፈው ሚሊኒየም ያስገኘልን አይነተኛ አስፈሪ ማስረጃ ነው፡፡

የኢትዮጵያ ህዝብ በቂ ምግብ አያገኝም የተወሰነ የምግብ ሰዓትም ስለሌለው አብዛኘው ህዝብ በቀን 3 ጊዜ የሚመገብበት ሁኔታ የለም አብዛኛው ህዝብ ቁርስ የሚባል ነገር አያውቅም ብዙውን ጊዜ ጠዋት ወደ ረፋዱ አካባቢ ከበላ እኩለ ቀን ላይ ምሳ አይበላም፡፡ በየቤተክርስትያኑና በየመስጊዱ፣በየጎዳናውና በየመንደሩ በልመና የተሰማሩት በርካታ ዜጎቻችን ቁርስ፣ ምሳ ወይም እራት የሚባሉትን የመመገቢያ ሰዓታት አይመለከታቸውም ለምነው ካገኙ ይበላሉ ካላገኙም ጦማቸውን ውለው ጦማቸውን ያድራሉ፡፡ በአለፉት 40 አመታት በምግብ እጦት ወይም ችጋር በሚሊዮን የሚቆጠሩ ኢትዮጵያውያን ሕይወታቸውን አጥተዋል፡፡ የአውሮፓ፣ አሜሪካና አውትራሊያ የስንዴና አልሚ ምግብ እርዳታ ባይመጣ ወይንም ባይደርስ የረሃብተኛው ቁጥርና የዜጎቻችን እልቂት እጅጉን በከፋ ነበር፡፡ በ1995 ዓ.ም 14.5 ሚሊዮን ኢትዮጵያውያን ወይም ከጠቅላላው ህዝባችን 22% የምግብ እርዳታ ተቀባይና ረሃብተኛ መሆኑ በሚሊኒየሙ ዋዜማ ከተከሰቱት አሳፋሪ ገጽታዎች አንዱ ነው፡፡ በርካታው የአገሪቱ ህዝብ የአልባሳት ችግር አለው፡፡ “ከቀዳዳ ይሻላል ጨምዳዳ” እያለ ህዝቡ በአብዛኛው የሚለብሳቸው ልብሶች በመርፌና ክር የተጣጣፉ ቁምጣ፣ ኮት፣ ሱሪና ቀሚስ ናቸው፡፡ ልጆችም አንድ ጊዜ የተገዛ አንድ ጥብቆ እየጣፉና እየጠቀሙ ዓመት ይለብሳሉ ብዙአኑ የኢትዮጵያ ህዝብ ሽሚዝ፣ ካኔተራና ሌሎች የውስጥ ልብሶች አይለብሱም ከጥቂቶች በስተቀር አብዛኛዎቹ ካልሲና ጫማ አያደርጉም በአንፃራዊ ደረጃ ያለልብስ እራቁታቸውን የሚኖሩ ኢትዮጵያኖች በደቡብና ምዕራብ ኢትዮጵያ አካባቢ ይገኛሉ፡፡

አብዛኛዎቹ ገጠር ነዋሪ ኢትዮጵያኖች «ቢጃማ» አንሶላና ፍራሽ አያውቁም አባወራዎች በጠፍር አልጋ ላይ ቁርበት አንጥፈው፣ ቡሉኮ፣ ከተገኘም ብርድ ልብስ ደርበው ሌሊቱን ያሳልፋሉ፡፡ ልጆች ደግሞ በመደብ ወይንም በቆጥ ወይም በወለል ላይ ሳር ጎዝጉዘው፣ ደበሎና ቁርበት አንጥፈው ይተኛሉ፡፡ የጨረቃ ብርሃን ከሌለ በገጠር የሚኖረው ህዝብ ሌሊቱን የሚያሳልፈው በድቅድቅ ጨለማ ነው፡፡

ሕዝቡ ምግቡን የሚያበስለው በእንጨትና በኩበት ማገዶ በመጠቀም ነው፡፡ የዘመናዊ ኢነርጂ ብሔራዊ አቅርቦት መጠን 7% አካባቢ ይሆናል፡፡ የኤሌክትርክ ሃይል መጠቀም ቀርቶ ብዙሀኑ በገጠር የሚኖሩ ኢትዮጵያኖች አንፖል ማብራትና ማጥፋት፣ ፍርጅና ሌሎች ተመሳሳይ የኤሌክትሪክ እቃዎች አይተውም ተጠቅመውም አያውቁም፡፡ የንፁህ የመጠጥ ውሃ አቅርቦትም እጅግ በጣም ዝቅተኛ ነው፡፡ ንፁህ የመጠጥ ውሃ የሚያገኘው ህዝብ ከጠቅላላው 30% አይበልጥም፡፡ ከጥቂት ከተሞች በስተቀር የፈሳሽ እና ደረቅ ቆሻሻ የማስወገድ አገልግሎት በኢትዮጵያ የለም ለማለት ይቻላል፡፡ አብዛኛው ህዝብ የሚፀዳዳው በየሜዳው ነው፡፡

አብዛኛው የኢትዮጵያ ህዝብ የሰው ልጅ እንደሰው የሚኖርበት ክፍሎች ያሉት መኖርያ ቤት የለውም ለዚህ አይነተኛ ማስረጃ ብዙ የሚሊኒየም ዓመቶች ያሳለፈችው በገጠሪቱ ኢትዮጵያ የምትገኙው ደሳሳ የጎጆ ቤት ናት፡፡ ድሃው ገበሬና ቤተሰቦቹ ቀኑን ሙሉ ሲጥሩ ሲግሩና ላባቸውን ሲያንጠፋጥፉ ውለው ሲመሻሽ ሁሉም ወደ ጎጆ ቤታቸው ይገባሉ፡፡

በዚች ባለአንድ ክፍል ጎጆ ቤት ውስጥ ነው ድሃው ኢትዮጵያዊ ከነቤተሰቡ በጋራ በመኝታ ቤትነት እያደረባት ለበርካታ ለሚኒሊየም ዓመቶች ሳይመቸው ሲኖርባት የነበረው፡፡ አሁንም በችግርና በእንግልት እየኖረባት ነው፡፡ በዚችው አንድ ክፍል ቤት ውስጥ ከድሀው ገበሬና ቤተሰቡ ጋር በጎች፣ ፍየሎች፣ ግመሎች፣ ጥጃዎች፣ ዶሮዎች፣ ቁንጫዎችና የወባ ትንኞች አብረው በጋራ ያድራሉ፡፡ ይውላሉ፡፡

ማደሪያ ብቻ አይደለም ምግብም በስሎ የሚበላው በዚችው አንድ ክፍል ጎጆ ቤት ውስጥ ነው። ከዚህም ብሶ ቤት ሳይኖራቸው በጫካና በሜዳ አካባቢ ተጠልለው እንደ እንስሳ የሚኖሩት ኢትዮጵያዊያን ቁጥር ጥቂት አይደለም ። ይህ ነው እንግዲህ በሁለት ወይም በሶስት የሚሊኒየም ጉዞ የኢትዮጰያ ሕዝብ ያገኘው አሳፋሪና አሳዛኝ የሕይወትና የኑሮ ገፅታ። "ኑሮ ካሉት መቃብር ይሞቃል" የሚለው አባባል የኢትጵያን ሕዝብ አስከፊና የሞት ሽረት ሕይወት በትክክክ የሚገልፅ ነው።

ይህ ዓይነቱን አስፈሪ የኢትዮጰያን ገፅታ ያስገኘ ሚሊኒየም በብሔራዊ ደረጃ ለማክበር ደፋ ቀና ሲባል የሕዝቧ የዘመናት የድኅነት ኑሮ የልማትና ፖለቲካ ችግሮች ከነመፍትሔ አቅጣጫቸው ተቀዳሚ ሥፍራ መያዝ ይኖርባቸዋል። የሚሊኒየሙ በዓል የኢትዮጰያን በጎ ገፅታ ለዓለም በማሳወቅ የነበረውን የአገሪቱን መጥፎ እይታ ለመለወጥ ተቀዳሚ ዓላማው እንደሆነ በአዘጋጆቹ ሲነገር ይሰማል። በየከተሞችና አካባቢያቸው ፓርክ ወይም መናፈሻ መሰራት የሙዚቃ ድግስና ሌሎች ቀላልና አስመሳይ ስራዎችን በማካሄድ ብቻ የኢትዮጰያን መጥፎ ገጽታዎችን መለወጥ አይቻልም። መጥፎ ገጽታችን ሊለወጥ የሚችለው በሕዝብ ተሳትፎ የሕዝብ መሠረታዊ የልማትና የፖለቲካ ችግሮች እውነተኛና ዘለቄታ ያለው መፍትሔ ሲያገኙ ብቻ ነው። ዓለም እኛ እራሳችንን ከምናውቀው በላይ ያውቀናል። በፖለቲካ ኢኮኖሚና ማሕበራዊ የእድገት ሚዛን ስንታይ እንደ ሀገርም ሆነን እንደ ሕዝብ የደሆች ደጎ ነን። በአክሱም፣ በላሊበላ፣ በአዲስ አበባ፣ በናዝሬት፣ በአዋሳ ወዘተ ያሉት ለማኞች ሀገር ጎብኝዎችን ወይም ቱሪስቶችን አስመርረዋል። መንግስትም በአቶ ስሞን መቻሌ የልመና ስብሰባዎችና በሌሎች የእርጥባን መጠየቂያ ዘዴዎች አማካኝነት የበለፀጉ ሀገሮችንና አለም አቀፍ የእርዳታ ድርጅቶችን በየግዜውና በየደቂቃው እየተማፀነ እንደሚኖር ዓለም ያወቀውና ፀሐይ የሞቀው ያለቀ ሀቅ ነው።

የ3000 ዓመት "ነፃነት" ወይም ከክርስቶስ ልደት በኋላ የሁለት ሚሊኒየም ጉዞ ያላት ሀገር ሕዝቦቿ ነፃነትና ስልጣን አላገኙም። የኢትዮጰያ ሕዝብ የፖለቲካ መብቶቹ ተከብረውለት አያውቅም። የብሔረሰቦች እኩልነት እስከ አሁን በኢትዮጰያ በተግባር አልታየም። በአሁኑ ጊዜ የብሔረሰቦች የእኩልነት ከፖለቲካ ፕሮፖጋዳነት አላለፈም። እንዲያውም ሁኔታዎች ተባብሰው አጠቃላይ እንቅንቃሴው ወደአሳፋሪ ጎሳዊና የዘረኝነት አገዛዝ እያመራ ነው። በአገዛዝ ስርዓቱ ውስጥ የህግ የበላይነት በአምባገነን መሪዎችና በፖለቲካ ካድሬዎች የበላይነት እየተተካ ነው። የፍትህ አካላቱ በፖለቲካ መሳሪያነት እያገለገሉ ናቸው። የሰብዓዊ መብቶች በከፍተኛ ደረጃ እየተረገጡ ይገኛሉ። በነፃነት የመሰብሰብ፣ የመፃፍና የመናገር መብቶች ታግደዋል። በአጠቃላይ በዚህ በኢትዮጵያ የሚሊኒየም ዋዜማ የግለሰብና የቡድን አምባገነነትን የአገሪቱ የመንግስት አገዛዝ ዘይቤ ሆኗው።

አፄዎቹና ንጉሶቹ በባህርያቸው ያገሪቱን ህዝብ ለበርካታ የሚሊኒየም አመታት ሲጨቁኑትና ሲረግጡት ኑረዋል። ደርግ በስመ ሶሻሊዝም ኢህአዲግ ደግሞ በኢስሙላ ዲሞክራሲ የኢትዮጵያን ህዝብ ስልጣን በመቀማት የገዙትንና እየገዙት ያሉት በዚህ አሁን ለማክበር ደፋ ቀና በሚሉለት የሚሊኒየም ዋዜማ ነው። የኢትዮጵያን ህዝብ የልማት፣ የዲሞክራሲ፣ የሰባዊ መብትና መልካም አስተዳደር ሁኔታዎች በዚህ በሚሊኒየም ዋዜማ ሆነን ስንገመግመው ኢትዮጵያውያን የሆነውን ብቻ ሳይሆን ሰው ለሆነ አካል በሙሉ ሁሉ የሚያሳዝን፣ የሚያሳፍርና አንገት የሚያስደፋ ጉዳይ ነው። እንደ ህዝብ ተርቧል፣ ስራ አጥቷል፣ የረባ ቤት የለውም። በጎሳ እየተከፋፈለ እየተጠላላና እየተጣላ ነው። ሁሉም የፍትህና የዲሞክራሲ ያለ እያለ በመጮህ ላይ ይገኛል። ስለዚህ አብዛኛው የኢትዮጵያ ህዝብ በፍፁም የድህነት አዘቅት እየተሰቃየ፣ እየተራበ፣ እየታመመ፣ እየታረዘ፣ የዲሞክራሲ አፈና እየተካሔደበት፣ እየታሰረ፣ እየተገደለ፣ የፍትህ ያለህ እያለ እየጮህና ሰብሃዊ መብቶቹ እየተረገጡ ባሉበት ወቅት የኢትዮጵያ ሚሊኒየም የአፍሪካ ሚሊኒየም ነው እያሉ ለማስመሰል መሞከር አቋሙ ፖለቲካ አይደለም። ያስገምታል።

የአትዮጰያ ሚሊኒየም ከፖሊቲካ ባሻገር ተቀባይነት ኢንዲኖረውና በአገር ቤትም ሆነ በውጭ ሀገር ያሉት ዜጎቻችን በሙሉ እንዲሳተፉበት መንግሥትና የበዓሉ አዘጋጅ አካላት አሁን የያዙትን ድግስ ወደ እውነተኛ ሕዝባዊ አከባበር መለወጥ ይገባቸዋል። የአከባበሩ ሂደት ከፖለቲካ ገለልተኛ ነው የሚለውን መመሪያ ቀይሮ ያገሪቱ የፖለቲካ

ችግሮች የሚፈቱበትንና መሠረት የሚጣልበት መሆን አለበት:: ለዚህም ሁሉም የፖለቲካ ኃይሎችን የሚያሳትፍ የብሔራዊ ሠላምና እርቅ ማዘጋጀትና ተግባራዊ ማድረግ ተገቢ ይሆናል:: ብሔራዊ ሰላምና ዕርቅን በኢትዮጵያ ሚሊንየም አከባበር ሂደት ውስጥ አብይና ተቀዳሚ ሥራ ማድረግ የበዓሉን ታሪካዊነትና ሕዝባዊነት በጉልሕ የሚያረጋግጥ ይሆናል:: ምክንያቱም የብሔራዊ ሠላምና ዕርቅ ክንዋኔ የሚሊኒየሙ በዓል በ1ኛ ደረጃ ሊስመዘግበው የሚችል ተጨባጭና ወቅታዊ የስራ ውጤት የሚሆን ነው:: ለብሔራዊ መግባባትና ዘላቂ ልቋትም መሰረት ይሆናል::

የሚሊኒየሙ የብሔራዊ ሠላምና ዕርቅ ክንዋኔ በምርጫ 97 አካባቢ የታዩትን የዲሞክራሲ ጥሩ ጅምሮችና ከዚያም በኃላ የተከሰቱትን የፖለቲካ ቀውሶች ማእከል አድርጎ መጀመር አግባብነት ያለው ሂደት ነው:: በግንቦት 97 ቅድመ ምርጫና በምርጫው ላይ የታየው የዲሞክራሲ ብርሃን ለብዙ ኢትዮጵያኖች ብዙና ታላቅ ተስፋ ፈንጥቆ ነበር:: ለዚህም የኢህአዴግ መንግስትና  ተወዳዳሪ ፓርቲዎች ለሳዩት ተሳትፎ፣ ውይይትና መቻቻል አድናቆት ሊቸረው ይጋባል:: አለመቀጠሉ በብሔራዊና ባለም አቀፍ ደረጃ ብዙ ሰዎችን አሳዝኗል:: ከምርጫው እለት በኃላ የታየው የዲሞክራሲ ብርሀን ደረጃ በደረጃ እየጨለመ በመሄዱ በስተ መጨረሻም ጭራሹንም ተዳፍኖ እነሆ በአሁኑ ግዜ ሀገሪቱ በከፍተኛ የፖለቲካ ቀውስ ውስጥ ትገኛለች:: ይህ ሁኔታ ነው በሚሊኒየም ዋዜማ የብሔራዊ ሠላምና እርቅ ጥሪና ክንዋኔ እንዲያካሂድ የሚያስገድደው:: የሁሉም ኢትዮጲያውያን ፍላጎትና ጥያቄ እንደሆነ ምንም ጥርጣሬ የለም::

በአብዛኛው ምርጫ 97 ከድምፅ ቆጠራው ጀምሮ ነፃና ፍታዊ አልነበረም:: የኢትዮጲያ ሕዝብ የመረጣቸውን ተወካዮቹን አላገኝም:: ምርጫው መጭበርበሩን በርካታ አካላት ኢሕአዴግም ጨምሮ ያምኑበታል:: ገዥው ፓርቲ ኢሕአዴግና ተወዳዳሪ ፓሪቲዎች ከ547 ጣቢያዎች በ299 የምርጫ ጣቢያዎች ወይም 55%  አካባቢ የሕዝብ ድምፅ መጭበርበሩን ተማምነዋል:: በዚህም መሠረት በ299 የምርጫ ጣቢያዎች በብሔራዊ ምርጫ ቦርድ አስተባባሪነት ምርመራ እንዲካሄድ በኢሕአዴግ፣ በቅንጅትና ሕብረት መካከል ሰኔ 3 ቀን 1997 ዓ.ም የስምምነት ፊርማ አድርገዋል:: አቶ በረከት ስሞኦን፣ ኢሕአዴግን፣ ዶ/ር መራራ ጉዲና ሕብረትን እኔ ደግሞ ቅንጅትን በመወከል በስምምነቱ ሰነድ ላይ መፈረማችንን ማስተወስ አስፈላጊ ነው::በስምምነታችን መሰረት በ299ኙም ምርጫ ጣቢያዎች ምርምራ ተካሒዶ በአብዛኛዎቹ ድጋሜ ምርጫ እንዲካሄድ ተደርጓል:: በጣም አስገራሚው ድጋሚ ምርጫው ከዋናው የግንቦት 97 ምርጫ በባሰ የድምፅ መጭበርበርና ዝርፊያ ተካሂዶበት ነበር:: በዚህም ምክንያት ብዙ ተስፋ ተጥሎበት የነበረው የነፃ ምርጫና ዲሞክራሲ ጭላንጭል በጅምሩ እንዲጠፋ መደረጉ በቡዙ አቅጣጫ ተረጋገጠ:: የአውሮፓ ሕብረት የምርጫ ታዛቢዎች ቡድንም የግንቦት 97 የኢትዮጵያ ምርጫ ዓለም አቀፉን ደረጃ የማያሟላ በመሆኑ ነፃና ፍታዊ አይደለም ብሎ በሪፖርቱ ገለፀ:: የኢትዮጵያ ህዝብን ድምፄን ተቀምቻለሁ የአልመረጥኳው ተወካዮች አያስተዳድሩኝም እያሀ መጮህ ጀመረ:: ተቃዋሚ ፓርቲዎችም ከብሄራዊ ምርጫ ቦርድ ኢህአዴግ አሸንፏአለሁ ብሎ ያወጀውን የምርጫ ውጤት አንቀበልም አሉ::

ቅንጅት ለአንድነትና ዲሞክራሲ ህዝቡን ስለምርጫው ውጤት ለመወያየት አቅዶ በአዲስ አበባ ወረዳዎችና የክልል ከተሞች በመንግስት እስኪከለከሉ ድረስ አካሂዷል:: በውይይቱም ህዝቡ ድምፄ ተቀምጧል፣ በኢህአዴግ አባላት በአብላጫ የተያዘው በፓርላማ የተመሰረተው በተጭበረበረ የምርጫ ውጤት ስለሆነ ፓርላማ አትግቡ የሚለውን ውሳኔ አብዛኛው አስተላለፈ:: ቅንጅትም የህዝቡን ስሜትና የላይላይ ምክር ቤቱን ውሳኔ መሰረት አድርጎ ፓርላማ ለመግባት 8 (ስምንት) የዲሞክራሲ ጥያቄዎችን አቀረበ:: ለ8ቱ የዲሞክራሲ ጥያቄዎች በጎ አገራዊ መልስ ስላላገኘ ለፓርላማ የተመረጡት አባላት የማይገቡ መሆኑን አሳወቀ:: ከዚህም ጋር በተያያዘ ቅንጅት በከፍተኛ ህዝብ ያሸነፈውን የአዲስ አበባ መስተዳደር ለመረከብ አልቻለም:: ከምርጫው ቀን በኋላ እየጨመረ የሄደው የፖለቲካ ውጥረት የኢትዮጵያውያንን ሁሉ ሃዘንና ስጋት ላይ ጥሏል:: ሰኔ 1 ቀን 1997 እና ጥቅምት 22 ቀን 1998 ዓ.ም አካባቢ ድምፄ ተቀምቷል፣ ምርጫው ተጭበርብሯል ብሎ በወጣው ህዝብ ላይ የተካሄደው የበርካታ ሰዎች ግድያና መቁሰል እንዲሁም ንብረት መጥፋት የሁላችንን ሃዘንና ፀፀት ነው:: ይህም በሚሊኒየሙ የዋዜማ አመታት ምርጫ 97 ያስከተለው ከፍተኛ የፖለቲካ ጠባሳ ነው::

ቅንጅት የህዝብ ድምፅ ይከበር ብሎ ባካሄደው ሰላማዊና ህዝባዊ እንቅስቃሴ ምክንያት ከፍተኛ አመራሮቹና አባሎቹ እንዲሁም የነፃ ጋዜጠኞች እና የሲቭል ማህበር አባላት ላይ መጠነ ሰፊ አፈናና እስራት መካሄዱ ሌላው የሚሊኒየሙ ዋዜማ አሳዛኝ የፖለቲካ ክስተት ነው። እነዚህ የሰላምና የዲሞክራሲ ሃዋርያ የሆኑ የቅንጅት አመራሮችና አባላት፣ የነፃ ጋዜጦች አዘጋጆችና የሲቪክ ማህበራት አላፊዎች የህገመንግስት ስርዓት የማፍረስ ሙከራ፣ በመንግስት ግልበጣና ክህደት፣ ዘር ማጥፋት በመሳሰለ የፈጠራና የሀሰት ክስ ተከሰው በቃሊቲና ሌሎች እስር ቤቶች እየተሰቃዩ ይገኛሉ። በአገር ውስጥና በውጭ አገር ያለው የኢትዮጵያ ህዝብና አለም አቀፉ ህብረተሰብ ተከሳሾቹ በሙሉ የፖለቲካና የህሊና እስረኞች ስለሆኑ ያህምንም ቅድመ ሁኔታ ባስቸኳይ እንዲፈቱ በየጊዜው ቢጠይቁና በተደጋጋሚ ቢያሳስቡም የኢህአዴግ መንግስት ግን አሻፈረኝ ብሎ የማናለብኝ ባህሪውን ቀጥሎበታል።

የኢትዮጵያ ህዝብ የቅንጅት አመራሮችና ሌሎች የፖለቲካ እስረኞች እንዲፈቱ በተለያየ ቦታና ጊዜ እየጠየቀና ተቃውሞውን እያሳየ ነው። በኢትዮጵያ ታላቁ ሩጫ፣ በስታዲየምና በሃይማኖት በዓላት ያቀረቡት ጥያቄዎችና ህዝባዊ ተቃውሞዎች አይነተኛ ማስረጃዎች ናቸው። ኢህአዴግም ባዘጋጃቸው በተለያዩ ስብሰባዎች ጭምር የምርጫ 97 የፖለቲካ እስረኞችን በመፍታት የአገሪቱ የፖለቲካ ቀውስ በሰላም እንዲፈታ በተደጋጋሚ ጥያቄና አስተያየት ለመንግስት ቀርቦለታል። በውጭ አገር የሚኖሩ ኢትዮጳውያንም በየወቅቱ የቅንጅት አመራሮችና ሌሎች የፖለቲካ እስረኞ እንዲፈቱ በርካታ ሰላማዊና ስልትና የዲፕሎማሲ ዘመቻዎች በአሜሪካና አውሮፓ ዋና ዋና ከተማዎች እንዲሁም በደቡብ አፍሪካና አውስራሊያ በማካሄድ ኢትዮጵያ ውስጥ ያለውን የፖለቲካ ቀውስና ሰብአዊ መብቶች ረገጣ ላለማቀፉ ህብረተሰብ እና መንግስታት አሳውቋል። ውጤትም አስገኝተዋል። ለአሜሪካ ኀንግረስ የቀረበው የኢትዮጵያ ዲሞክራሲ ስርዓት ግንባታና የተጠያቂነት ረቂቅ ህግ የፖለቲካ እስረኞች ያለአንዳች ቅድመ ሁኔታ እንዲፈቱ የሚጠይቅ ነው። ይኸውም በውጭ አገር የሚኖሩ ኢትዮጵያኖች ያለሰለሰ ጥረት አድርገው ያስገኙት ውጤት ነው። በተመሳሳይ ሁኔታ የአውሮፓ ህብረትና ፓርላማው እንደዚሁ የቅንጅትና ሌሎች የህሊና እስረኞች ባስቸኳይ እንዲፈቱ የሚጠይቅ ውሳኔ አስተላላፏል። በአለም አቀፍ ደረጃ የሚገኙ የሰብአዊ መብት ጥበቃ አራማጅ ድርጅቶች በቃሊቲና በሌሎች እስር ቤቶች ያሉት የፖለቲካና የህሊና እስረኞች እንዲፈቱ በየጊዜው ያሳስባሉ። በአንፃሩ የኢህአዴግ መንግስት ከአገር ውስጥ በኢትዮጵያ ህዝብ ለሚቀርቡለት የይፈቱልኝና የሰላም ጥያቄዎችም ሆነ በውጭ አገር በሚደረገው የብሄራዊ ዕርቅ ግፊቶች ምንም አይነት በጎ መልስ ባለመስጠቱ የአገሪቱ የፖለቲካ ቀውስ አሳሳቢነት በመጨመር ላይ ነው። በየአካባቢው በተለያዩ የትግል ስልቶችና ድርጅቶች የሚቀርበው የዲሞክራሲ ጥያቄ በመንግስት በኩል የሚሰጠው መልስ እስራትና ግድያ በመሆኑ የፖለቲካ ቀውሱን ወደከፍተኛ ደረጃ እያሳደገው ይሄዳል እንጂ ዘላቂነት ያለው ሰላምና ልማት አያመጣም። የኢህአዴግ መንግስት በፖለቲካ ጥላቻ ላይ የተመሰረተ የእስራትና ግድያ ስትራነጅውነተ ቀይሮ የመቻቻል ፖለቲካና አገራዊ ሰላም በውይይት እምዲመጣ በሩን በሰፊው መክፈት ይኖርበታል። በኢትዮጵያም ፖለቲካ ያገባኛል የሚሉም የፖለቲካ ድርጅቶችም ከጥላቻና በቀል ፖለቲካ ተላቀው ለዘላቂና እውነተኛ የዲሞክራሲ ስርዓት ግንባታ ለመስራት ከመቸውም ጊዜ የበለጠ ዝግጁ መሆን አለባቸው። ሁሉም የፖለቲካ አካላት አላማና ራዕይ ዲሞክራሳዊት እና የበለፀገች ኢትዮጵያን መገንባትና ማየት ስለሆነ አሁን ያለው የፖለቲካ ጥላቻና ጠብ ወደ ብሄራዊ ዕርቅና መግባባት መለወጥ ይቻላል። ለዚህም የኢትዮጵያ ሚሊኒየም በዓል አመቺኛ ልዩ የታሪክ አጋጣሚ ነው። ሚሊኒየሙ ከምንም በላይ በታሪክ ሊታወስና ህዝባዊ ሊሆን የሚችለው የብሄራዊ ሰላምና እርቅ ሲያስገኝ ብቻ ነው።

በቃሊቲ በታሰሩት የቅንጅት አመራሮችና በመንግስት መካከል በአገር ሽማግሌዎች አማካኝነት የተካሄደው የዕርቅ ድርድር አስፈላጊና ሁሉንም ወገን በእጅጉ የሚያስመሰግናቸው ነው። በተለይ የአገር ሽምግሌዎቹ የወሰዱት የማደራደር ተነሳሽነትና ያደረጉት ከፍተኛ ጥረት እጅግ በጣም የሚደነቅ የቅን ዜጎች ተግባር በመሆኑ ከፍተኛ ከበሬታና ምስጋና ይገባቸዋል። በአገር ሽማግሌዎች አማካኝነት የዕርቅ ድርድሩ መጀመሩና በተደጋጋሚ መካሄዱ የሁለቱንም ተስማሚ ወገኖች ሀገራዊ ሃላፊነት በጥሩ ጎን የሚጠቁም ቢሆንም የኢህአዴግ መንግስት በስተመጨረሻ ያሳየው ግትር አቋሙ በጣሙን አሳዛኝ

ነበር:: የኢህአዴግ መንግስት የትልቅነት ባህሪና ሃላፊነት መውሰድ ሲገባው የፈፀመው ክምር ስተቶችን ወደ ቅንጅት መግፋቱ ለከፍተኛ ትዝብት ያዳርገዋል:: በአሁኑ ጊዜ በተለይ በኢትዮጵያ ሚሊኒየም ዋዜማ ትልቅ ቁምነገር መሆን ያለበት ያለፉ ስህተቶችን አንዱ በሌላው ማሳበብ ሳይሆን ስተቶቹ ትክክል አለመሆናቸውን ከልብ ተማምኖ ወደ ብሄራዊ ሰላምና ዕርቅ ማምራት ነው:: የተፈፀሙትን የፖለቲካ ስህተቶች ከበቀልና ወቀሳ ነፃ በሆነ መንገድ ተጣርተው ወደፊት በምንም ሁኔታ እንዳይደገሙ እና ትምርታዊ እነዲሆኑ ብቻ ማድረግ የብሄራዊ ሰላምና ዕርቁ በአስተማማኝ የመግባባት መንፈስ ላይ ይመሰረታል:: እስካሁን በአገሪቱ የታዩትን የፖለቲካ ቆሻሻዎች ወደኋላ ወርውረን በህዝባዊ መፈቃቀርና አንድነት አዲሱን ሚሊኒየም መቀበል የሁላችንም ግዴታ መሆን አለበት::

ኢትዮጵያ በአሁኑ ጊዜ የምትገኝበት የፖለቲካ ቀውስ በአስተማማኝ ሁኔታ ሊፈታ የሚችለው በውይይት፣ በሰላምና በዕርቅ መሆኑን በጉዳዩ ያገባኛል የሚሉ አካላት መንግስትም ጭምር የሚያምንበት መሆኑን በተላላዩ ጊዜያት ተናግረውታል:: መግለጫም ሰጥተዋል:: ትልቁ ችግር የተናገሩትንና ያመኑትን የሰላም መፍትሄ ተግባራዊ ማድረጉ ላይ ነው:: በዚህ አንፃር በአገሪቱ የተከሰቱትን የፖለቲካ ቅራኔ በብሄራዊ ሰላምና ዕርቅ እንዲፈታ በሚሊኒየሙ ዋዜማ ሁላችንም ያገኘነው ትልቅ ታሪካዊና ልዩ አጋጣሚ ነው::

የኢትዮጵያ ሚሊኒየም በዓል ከምንም በላይ መሰራት ያለበት በብሄራዊ ሰላም፣ ዕርቅና ህዝባዊ መግባባት ላይ ነው:: የብሄራዊ ሰላምና ዕርቅ በአገራችን ካልታየ ብሄራዊና ህዝባዊ መግባባት አይኖርም:: የኢትዮጵያን መጥፎ ገፅታም በሂደት መለወጥ አይችልም:: አገራዊ ሰላም፣ ፖለቲካዊ ዕርቅና ህዝባዊ መግባባት ከተፈጠረ የኢትዮጵያ መጥፎ ገፅታ ማለት ድህነትን፣ ረሀብን ወ.ዘ.ተ በአጭር ጊዜ ውስጥ መለወጥ ይቻላል:: ሕንድ ከችጋርና ረሃብ ተላቃ የአለም ትልቁ ኢኮኖሚ ለመሆን የምትሮጠው ባለፉት 50 ዓመታት በአገኘ ችው ሰላምና ዲሞክራሲ ነው:: ደቡብ ኮሪያ የአለም 10ኛ የኢኮኖሚ የበለፀገች አገር መሆን የቻለችው ከ50 ዓመት በፊት ከጦርነት ተላቃ ሰላምና ዕርቅ በማውረዷ ነው:: ኢትዮጵያና ደቡብ ኮርያ ከ50ዓመት በፊት እኩል የልማት እድገት ነበራቸው:: ደቡብ ኮርያ በሰላም፣ በስራና ሕዝባዊ መግባባት በአጭር ጊዜ የበለፀገች አገር ስትሆን ኢትዮጵያ ግን በሰላም፣ ፍትህ፣ ዲሞክራሲ እኩልነትና ሕዝባዊ መግባባት እጦት የድህነትና ረሃብተኞች ምሳሌ ሆነች:: በዚህ አሳፋሪ ድርጊታችን ሁላችንም በተለይ የተማረውና በአመራር ላይ የነበርነው ተጠያቂዎች ነን:: ስለዚህ እንደ ህዝብ፣ እንደ መንግስት፣ እንደ ተማሪ ዜጋ የአሳየውን ክምር አገራዊ ድክመቶችና የፈፀምናቸውን በርካታ ስህተቶች በሃቅ መርምረንና አርመን፣ አዲስ ብሄራዊ የሰላም፣ የዕርቅ፣ የመግባባት፣ የፍትህ፣ የዲሞክራሲና የጠንካራ ሠራተኝነት መንፈስ በአዲሱ ሚሊኒየም መፍጠር አለብን::

የኢትዮጵያ ሚሊኒየም በእኩልነት ላይ የተመሰረተ አዲስ የሕዝብ አንድነት መንፈስ ለማራመድ አመቺና ጥሩ የታሪክ አጋጣሚ ፈጥሯል:: ሚሊኒየሙን ምክንያት በማድረግ ፓርኮች እንደሚሰሩ፣ ሓውልቶች እንደሚቋቋሙ፣ ዛፎች እንደሚተከሉና ሌሎች ተመሳሳይ ተግባራት እንደሚከናወኑ በአዘጋጆቹ በተደጋጋሚ ተነግሯል:: እነዚህ የሚሊኒየሙ መሪ ድርጊቶች በአመዛኙ ሊኖራቸው የሚችለው ቁሳዊ ገፅታና ትውስታ ብቻ ነው:: ሕዝባዊና መንፈሳዊ ነፀብራቅ የላቸውም:: የሚሊኒየሙ ፓርክ የሚሊኒየሙ ዛፍ ከመባል አያልፍም ፓርኮቹም ሆነ ዛፎቹ ከዘመን ማስታወሻነት አልፈው ከበስተዋላቸው የሚይዙትም ሆነ የሚያስተላልፉት ሕዝባዊ መንፈስና አገራዊ መልዕክት አይኖራቸውም:: የሚሊኒየሙ አከባበር ሕዝባዊና አገራዊ ተልዕኮ እምዲኖረው ከተፈለገ በሚሊኒየሙ አማካይነት የሚከናወኑ ቋሚ ስራዎች የሰላም፣ የዕርቅ፣ የእኩልነት፣ የፍትህና የዲሞክራሲ ባህሪና ስያሜን ማስተጋባት ይኖርባቸዋል:: የሰላምና የዕርቅ ፓርኮች፣ የእኩልነትና አንድነት ሓውልቶች፣ የፍትህና የዲሞክራሲ አደባባዮች በሚሊኒየሙ አከባበር ሂደት ውስጥ መሥራትና መሰየም ጥሩ አጋጣሚና ጊዜ ነው:: በብሄራዊ ሰላምና ዕርቅ አንፃርና ሁለት ዛፍ በ2000 በሚለው መርህ አንድ ዛፍ ለሰላም፣ አንድ ዛፍ ለእኩልነት፣ አንድ ዛፍ ለፍትህና አንድ ዛፍ ለዲሞክራሲ በሚሉት ስያሜዎች ቢታጀቡና ዛፎቹ ቢተከሉ የኢትዮጵያን ሚሊኒየም አከባበር ፍፁም ሕዝባዊና ታሪካዊ ያደርጉታል::

የኢትዮጵያ መጥፎ ገፅታ የተለወጠው፣ ፍትህና ዲሞክራሲ የመጣው፣ አስተማማኝ ህዝባዊ ልማት የተገኘው በሁለተኛው የኢትዮጵያ ሚሊኒየም መቋጫ በተገኘ ው ብሄራዊ ሰላምና ዕርቅ ነው፣ እየተባለ ሁሉም የሚሊኒየሙ ቋሚ ማስታወሻዎች ሁልጊዜ በታሪክ ይዘከራሉ:: በዚህም መሰረት የኢትዮጵያ ሚሊኒየም የምናካሂደው የብሄራዊ ሰላምና ዕርቅ ውድ አገራችን ለሆነችው እናት ኢትዮጵያ አስተማማኝ እድገት መሰረት የሚኖርና የሚራመድ በመሆኑ በተግባራዊ ሁሉም በተለይ መንግስት ልዩ ትኩረት ሊሰጠው ይገባል:: ሁላችንም ከእልህና ከመጠፋፋት ባህሪያችን ተላቀን ሰላምና ዕርቅ ማውረድ አለብን:: ለዚህም የመጀመሪያው ርምጃ መሆን የአለበት የታሰሩት የቅንጅትና ሌሎች የፖለቲካ እስረኞች እንዲፈቱ በአገር ሽማግሌዎች በተደጋጋሚ የተከናወነው አኩሪ የዕርቅ ጥረት ግቡን እንዲመታ ማድረግ ነው:: በዚች አገር በፖለቲካ ቅራኔ ምክንያት የብዙ ሰዎች ደም ፈሷል:: ብዙ ዜጎች ለዓመታት በእስራት ያለአግባብ ተሰቃይተዋል:: በርካታ ኢትዮጵያውያን ውድ አገራቸውን ጥለው ተሰደዋል:: ሕዝቡ ለብዙ አመታት እውነተኛ ሰላምና ደስታ አጥቷል:: ይህ አይነቶች አሳዛኝና አሳፋሪ ድርጊቶች በብሄራዊ ሰላምና ዕርቅ አማካኝነት በአዲሱ ሚሊኒየም መቆም አለባቸው:: በዚህ ትውልድ ማብቃት ይኖርባቸዋል:: ለዚህም ሕዝብ፣ መንግስትና ተቃዋሚ ፓሪቲዎች በአንድነት እንነሳ ! እንተባባር ! ውድ እናት ኢትዮጵያን እናድናት! እናልማት! እናበልፅጋት! እያልኩ የሚሊኒየሙን የብሄራዊ ሰላምና ዕርቅ አገራዊ ጥሪ በሁሉም ሰላም ወዳድ ስም ለሁሉም በታላቅ ትህትና አቀርባለሁ:: ለኢትዮጵያ የሚበጃት የእኛ የሕዝቦቿ ሰላምና መፈቃቀር ብቻ ነው::

በቅንነትና በንፁህ ህሊና እንተግብረው !!!!!!!!!!!!!!

- ኢትዮጵያ እጆቿን ወደ እግዚአብሔር ዘርግታለች::
- ኢትዮጵያ እጆቿን ለብሄራዊ ሰላምና ለዕርቅ ወደ እኛ ዘርግታለች!!!!!

ከቃሊቲ ማረሚያ ቤት
<u>ኢንጅነር ግዛቸው ሽፈራው</u>